# -ኃይሌ ገ/ሥላሴ ስብሰባውን አቋዋረጠ ታማኝ በየነና ኤልያስ ክፍሌ ከወያኔ ሊታረቁ ንግግር ጀመሩ

*ኢትዮጵያ ዛሬ ዜና፡-* አዲስ አበባ ላይ የተጀመረው የወያኔን ተቃዋሚዎች የማግባባት ስራ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመዝለቅ ከትላንት በስቲያ አዲስና ብዙዎችን ያስገረመ ሁኔታ ተከስቱአል።

ከዲሴምበር 11 — 2007 አንስቶ ለሶስት ቀናት በዘለቀውና ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ኮስሞስ ክለብ (Cosmos Club) በተካሄደው የመጀመሪያ ዙር ስብሰባ ታርቀው እንዲገቡ ከተጋበዙት መሃል በዋንኛነት ታማኝ በየነ (ኢቲኤን ቲቪ)፣ ኤልያስ ክፍሌ ( ኢትዮጵያን ሪቪው) ፣ እና አበበ በለው ይገኙበታል። ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎችም ሲገኙ በተቃውሞ መድረኩ ስማቸው የሚነሳ ሰዎችን የማካተቱ ስራ ሰፊ እንደሆነም ለማወቅ ተችሉአል። በቀዳሚነትም በቅንጅት መሪዎች መሃል የተፈጠረውን ልዩነት በመጠቀም በዶ/ር ብርሃኑ ለሚመራውና ለዘብተኛ አቋዋም ለማሳየት ፈቅዱአል የሚባለው ቡድን ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦችን ከወያኔ ጋር ማስታረቁ ቅድሚያ ተስጥቶታል ተብሉአል።ከዚህ ጋር ተያይዞ የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው በቅርቡ ወደ ሰሜን አሜሪካ አቅንተው የነበሩት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ም/ል ጠ /ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ እና የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አያሌው ጎበዜ በዋሽንግተን ዲሲ ከታማኝ በየነ ጋር ተገንኝተው ነበር። የውይይቱ ርዕስ ምን እንደነበረ ባይመለከትም ነግግሩ አሁን የተጀመረው ሽምግልና አካል እንደሆነ ተገምቱአል።

ይህን ተልዕኮ ከአዲስ አበባ ይዘው የመጡት በቀዳሚነት የቅንጅት መሪዎች ይቅርታ ጠይቀው እንዲፈቱ ያስደረጉት ፕ/ር ኤፍሬም ይስሃቅ ናቸው ይባል እንጂ ከርሳቸው ጋር ታዋቂው አትሌት ኃይሌ ገ/ ሥላሴ እንደነበርም ታውቁአል። ከነርሱ በትጨማሪም ፓስተር ዳንኤል እና የቅንጅት አለማቅፍ ኮሚቴ አመራር አባል የነበሩት ኢ/ር ሞገስ ገ/ማርያምም ተሳትፈዋል። ይሁንና ኃይሌ ገ/ ሥላሴ በሽምግልናው ጥሪት ከሶስት ሰአት ላልበለጠ ጊዜ እንደቆየና ሌላ ስራ አለኝ በሎ እንደሄደ ለማወቅ ተችሉአል።ከሽምግልናው በሰተጀርባም በቅረቡ ከካሊፎርኒያ ለቀው ወደ አዲስ አበባ በመግባት በወርልድ ባንክ ስራ ተስጥቶአቸው የሚሰሩትና የበረከት ስምዖን የቅርብ ወዳጅ የሆኑት ግለሰብ እንደሚገኙ ተሰምቱአል። በዚህና በስብሰባው በተሳተፉ ሌሎች እጩዎች ዙሪያ ወደፊት ተከታትለን እንመለስበታለን።

እነዚህ አሁን ከወያኔ ጋር እርቅ አውርደው በጋራ እንዲሰሩ የተጠየቁት ግለሰቦች በአሁኑ ወቅት በተቃዋሚነት ራሳቸውን በየመድረኩ እያሳዩ እንደሚገኙ ይታወቃል።

ምናልባት ይህ ጥረት ገቢራዊ ከሆነ ወዶ ከገባው ድምጻዊ ሰለሞን ተካልኝ ቀጥሎ የወያኔን ጎራ የሚቀላቀሉ የመድረክ ሰዎች ይሆናሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን የሚሰጡ ታዛቢዎች ታማኝ በየነ ከሼህ አላሙዲ ጋር ከነበረው ትሥሥር አኩአያ እስካሁን ድረስም ምነው ዘገየ እያሉ ይተቹታል። ሌሎቹን በተመለከት ደግሞ ራሳቸውን ተቃዋሚ ነን አሉ እንጂ እስካሁን አገዛዙን የሚያስጨንቅ ምንም ስራ አልሰሩም ይሉአቸዋል። ይሁንና ይህን መሰሉ ስራ ለወያኔ እንደስኬት እንደሚቆጠርለት የሚጠቁሙ ቢኖሩም ብዙዎች ግን በአሁኑ ወቅት እጩ ግለሰቦቹ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ አኩአያ አይደነቁም። በተለይም

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ “መቻቻል ይቻላል” በሚል በጀመሩት አዲስ ፈሊጥ ግለሰቦቹ ሳይጠየቁም ለመወዳጀት እየተማጠኑ ነበር እያሉ የሚተቹ በዙ ናቸው። ምናልባትም ይህ ጥረት ወደ ቪኦኤ ጋዜጠኞችም ሊቀጥል እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

አንዳንድ የተቃውሞ መሪዎችን በአክራሪነት የሚወነጅለው አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የተወሰኑትን ደግሞ በለዘብተኛና በታማኝ ተቃዋሚነት ይዞ መጉአዝ እንደሚሻ በተደጋጋሚ ሲያሳውቅ መቆየቱ አይዘነጋም። ይህ የአሁኑ እንቅስቃሴም የዚህ አካል ሊሆን እንደሚችል የሚገምቱ ታዛቢዎች አገዛዙ በዚህ የልዩነት መዛመት ላይ ወያኔ እጁ የለበትም ለማለት የሚያስደፍር መረጃ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማግኘት እንዴት ይቻላል ሲሉ ይተቻሉ።